# ብርቱካን ሚዴቅሳ - አይበገሬ ኢትዮጵያዊት

በአለማየሁ ገብረማርያም (ፕ/ር)

- ብርቱካን ሚዴቅሳ ቂም በቋጠረ አምባገነን ለእድሜ ልክ እስራት ተዳርጋለች፣ ነገር ግን አልተበገረችም::
- ብርቱካን የምሬትና የእምባ ወደሆነው ድቅድቅ ጨለማ ጉድጓድ ተወርውራለች፣ ሆኖም ፍንክች አላለችም::
- ብርቱካን ተደብድባለች እንዲሁም ደምታለች፣ ሆኖም አልተንበረከከችም:: - የአገዛዙ ባለስልጣናት በብርቱካን ላይ አላግጠዋል፣ አሹፈውባታል፣ ነገር ግን ደግነቷ አልተለያትም::
- ብርቱካን ተወግዛለች፣ ነውር ተጽፎባታል፣ ተገፍትራለች እንዲሁም ተጐትታለች፣ ሆኖም አልፈራችም::

ኢትዮጵያ በቅጥረኛ ደፍጣጭ ወታደሮች ስር ነች::

አይበገሬዋ ብርቱካን!

አይበገሬዋ ኢትዮጵያ!

ታህሳስ 29/2008 ይታወሰኛል:: የዛሬ አንድ ዓመት አካባቢ፣ በኢትዮጵያ የ3ሺህ ዓመት ታሪክ ውስጥ ብቸኛዋ ሴት የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ እየተገፈተረች በኃይል ወህኒ የተወረወረችበት ቀን:: የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ካውንስል መስራችና የቀድሞ ሊቀመንበር የሆኑት ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፣ ለወንጀሉ የአይን እማኝ ናቸው:: አራት በጉልህ የማይለዩ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወንጀሉ የተፈጸመበትን ስፍራ በወረሩበት ወቅት፣ እርሳቸው ከብርቱካንና ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ከአንድ ቢሮ ሕንጻ ደጃፍ በመነጋገር ላይ እንደነበሩ ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ተናግረው ነበር:: በግምት አስር የሚደርሱ ታጣቂ ሰዎች ከተሽከርካሪዎቹ ዱብ ዱብ ብለው ወርደው ብርቱካንን ከበቧት:: እፍን አድርገው ይዘዋት በመጎተት ወደአንደኛው ተሽከርካሪ አስገቧት:: ከወንበዴዎቹ አንደኛው፣ 80 ዓመት የሚሞላቸውን ፕ/ር በያዘው መሳሪያ ሰደፍ አበክሮ ደቆሳቸው:: ወዲያው በሴኮንደች ውስጥ፣ ብርቱካን ወደ አሰቃቂው የቃሊቲ ወህኒ ቤት ተወሰደች፤ ፕ/ሩ ደግሞ ወደ ሆስፒታል::

ብርቱካን ከመንገድ ታፍና እስከተያዘችበት ጊዜ ድረስ የነበሩ የነገሮች አካሄድ እውነታዎች ለክርክር የሚቀሩ አይደሉም:: በታህሳስ 10/2008፣ «የፌዴራል ፖሊስ

ኮሚሽነር» ብርቱካን ወደ እርሱ ቢሮ እንድትመጣ ትዕዛዝ የሚያደርሱላትን ሁለት የወረዳ 12 ፖሊሶችን አስላከባት:: ምናልባት ስለ ፖለቲካ ፓርቲዋ ሊያወራት ፈልጐ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ቢሮው ሄደች:: ሆኖም ያስጠራት በ2007 ከእስር እንድትፈታ ስላስደረጋት ይቅርታ ነበር:: ጉዳዩን አስመልክቶ እርሷን ለመመርመር ምን ሥልጣን እንዳለው ጠየቀችው:: ነገር ግን ተሳለቀባት:: እርሷም ከቢሮው ወጣች:: በታህሳስ 24/ 2008፣ «ኮሚሽነሩ» ቢሮው እንድትቀርብ ካስደረገ በኋላ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጣት፤ የተሰጣትን ይቅርታ አልተቀበልኩት ብላ በመካድ በሲዊድን አገር ተናግራዋለች የተባለውን ንግግሯን እንድታስተባብል፣ አለበለዚያ ተፈፃሚ የሚሆን እስር እንደሚጠብቃት የሚያስገነዝብ ነበር ማስጠንቀቂያው::

ብርቱካን ይቅርታ መቀበሏን በጭራሽ ክዳ አታውቅም:: ለተወሰኑ የደጋፊዎች ቡድን ባደረገችው ንግግር ይቅርታ ተብዬውን ስለመቀበሏ ክዳለች በተባለችበት ሲውዲን፣ የተናገረችው ይቅርታ በመስጠቱ ዙሪያ ስላሉ ሕጋዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ብቻ ነበር:: በሕገ-ወጥ መንገድ ከመታሰሯ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ «ቃሌ» በሚል ርዕስ ይፋ በተደረገው ጽሁፏ፣ ይቅርታ ተብዬውን መቀበሏን ሙሉ በሙሉ አረጋግጣለች:-

**«በሰኔ 22/2006፣ ለብሔራዊ እርቅ በሚል፣ ሽማግሌዎች እንድንፈርመው ባሳመኑን ሰነድ ላይ መፈረሜን አልካድኩም:: እኔ ራሴ የፈረምኩበትንና ያካተታቸውን የተቀበልኩትን የይቅርታ ሰነድ እንዴት ክደሻል ሲባል ይችላል? የተቀበልኩት? እንዴት ያ ወንጀል ይሆናል? ስህተቱ የቱ ጋር ነው?»**

የጉዳዩ እውነታ ይስሙላው ፍ/ቤት ጥፋተኛ ላደረጋትና ላልተፈጸመ ሀሰተኛ ወንጀል ነበር ሀሰተኛ ይቅርታ የተሰጣት:: «ማንኛውም ምክንያት አምባገነኑን ያገለግላል» ነው የሚባለው፤ አቶ መለስ ዜናዊ፣ ብርቱካንን ያሰረበት ምክንያት ይቅርታ መቀበሏን በመካዷ ነው ማለቱ በራስ አእምሮ ላይ እንደመሳለቅ ነው:: ተጨባጭ እውነታዎቹ ምንድናቸው፣ ብርቱካን በ2010 ምርጫ እንዳትፎካከር እርሷን ሽባ ከማድረግ እና የእርሱን አምባገነንነት ለመቃወም ሰፊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት የመገንባት ጥረቶቿን ከማኮላሸት ጋር የተያያዙ ናቸው:: መለስ፣ ብርቱካን በግልጽ አሻፈረኝ ማለቷ እርሱን እንደናቀች አድርጎ መውሰዱ አያጠራጥርም::

**ብርቱካን ሚዴቅሳ ማን ነች?**

በቅርቡ፣ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ለይስሙላው ፓርላማው፣ ብርቱካን ራሷን እንደሰቀለችው ዶሮ ነች ብሎ ተናግሮ ነበር:: እርሷን ለመግለጽ የእንስሳት ምሳሌያዊ አገላለጽ መጠቀም ግድ ካለን፣ ብርቱካን በትክክል የምትገለፀው የጅብ መንጋ እንደ ምትፋለም አንበሳ ነው:: ራሷን የምትገልጸው ሁሌም ለሕግ የበላይነት፣ ለነፃነት፣ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች የምትቆም ተራ ሴት አድርጋ ነው:: ጠላቶቿን በሚገባ ትረዳቸዋለች:: በሕገ-ወጥ መንገድ ከመታሰሯ ከቀናት በፊት፣ የአዲስ ነገር (አምባገነኑ

*በገለልተኛው ፕሬስ ላይ የከፈተውን ጦርነት ተከትሎ በቅርብ የተዘጋች ሳምታዊ ጋዜጣ) መስራች አዘጋጆች አንዱ ለሆነው ጋዜጠኛ አብይ ተክለማርያም፡-*

**«የወረቀት ሳይ ነብር መሆናቸውን ማወቅ አለብህ፡፡ ደካሞች ናቸው፤ ሆኖም ጠንካራ መስለው ለመታየት ይሞክራሉ፡፡ ከሶስት ዓመት ልጇ ጋር፣ በእነርሱ ብርቱ የቀን በቀን ክትትል ስር የምትኖርን ሴት ማሰር ጥንካሬያቸውን የሚገልጽ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ . . . ሰዎችን አስገድደው ለቤተሰባቸውና ለማሕበራዊ ግዴታዎቻቸው ታጋች ያደርጓቸዋል፡፡»** ብላ ነግራው ነበር፡፡

*እናም፣ እውነተኛዋን ብርቱካን ለማወቅ ለሚፈልግ ምላሹ ቀላል ነው፡፡ ብርቱካን ማለት ካለአንዳች ማንገራገር ከቤተሰብ ነፃነትን፣ ከልጅ አገርን እና ከሁሉም በላይ ደግሞ እርሷን ከወለዷት እናቷ በፊት እናት ኢትዮጵያን የመረጠች የኢትዮጵያ አናብስቶች አንበሳ ነች፡፡ ብርቱካን ማለት ድንቅ ስብዕና የተላበሰች፣ ራሷን ዝቅ አድርጋ የምትመለከት፣ ቆፍጣና፣ ለመርህ ተገዥና አመክንዬ የተላበሰችና አገናዛቢ ኢትዮጵያዊት ነች፡፡ በሕገ-ወጥ እስሯ አንደኛ ዓመት ላይ ሳለን፣ ለልዩዋና ለታላቋ ኢትዮጵያዊት የፖለቲካ መሪ ያለኝን አክብሮት መገለጽ ለእኔ የተለየ ክብርና እድል ነው፡፡*

*እንደእኔ እምነት፣ እያንዳንዱ የተመረቀ ሕዝብ ስቃዩንና ሕመሙን፣ ያለበትን ጉስቁልናና የወደፊት የዕድገት ደረጃውን የሚያሳይለት ግለሰብ በእግዚአብሔር ተችሮታል፡፡ እንዲያ ያለ ግለሰብ የጠፋና ተስፋ የቆረጠ ሕዝብን፣ ከአስከፊ የግጭትና እርቅ ከራቀው ጨለማ ወጥቶ ወደነፃነት፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ ብርሃን እንዲገባ ለማስቻል ወደመሪነት የሚለወጥ ነው፡፡*

*በደቡብ አፍሪካ፣ ኔልሰን ማንዴላ በዘርና በቀለም የተከፋፈለውን የደቡብ አፍሪካውያንን የፖለቲካ ሁነት በመጠገን፣ ሕዝባቸውን ወደተሳካ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ መርተዋል፡፡ በሕንድ፣ ማህተማ ጋንዲ በእጃቸው ምንም ሳይይዙ፣ በልባቸው ፍቅርንና በመላ የሰውነታቸው ጅማቶች ደግሞ እምቢተኝነትን ብቻ በመያዝ፣ አገራቸውን ከቅኝ አገዛዝ ወረርሽኝ ነፃ አውጥተዋታል፡፡ በዩ.ኤስ አሜሪካ ደግሞ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ የአሜሪካውያንን ሂሊና ቆንጥጦ በመያዝ የዘረኝነትና የመድሎ መንትያ ጋኔኖችን ነቅለው እንዲያወጧቸው ረድተቿል፡፡ በበርማ (በአሁኗ ማየንማር)፣ ኦንግ ሳን ሱ ቺ ለዓመታት በቁም እስር በመማቀቅ ላይ ትገኛለች፤ ያም ሆኖ ለእያንዳንዱ ምየንማርያዊ የተስፋና የነፃነት ጮራ ተደርጋ ነው የምትታየው፡፡ ምህረት የለሹንና ጨካኙን አምባገነን በመጋፈጧ ዛሬ ወሂኒ ቤት በመማቀቅ ላይ የምትገኘውን ብርቱካን ሚዴቅሳን ኢትዮጵያ በማግኘቷ ተባርካለች፡፡ ብርቱካን፣ አንድ ቀን ሕዝቧ በነፃነት እንዲኖር እና የነፃነት ቱርፋቶችን እንዲያጣጥም በሚል የራሷን ነፃነት በፍቃደኝነት ሰውታለች፡፡*

ብርቱካንን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘሁዋት፣ በመስከረም 9/2007 ወደ ሰሜን አሜሪካ የመጣውን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (ቅንጅት) ልዑካን ቡድን በመምራት ከዋሽንግተን ዲ.ሲ. ወጣ ብሎ በሚገኘው ዳላስ አየር ማረፊያ በደረሰችበት ወቀት ነበር:: በወቅቱ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ ዶ/ር ሃይሉ አርአያ፣ አቶ ግዛቸው ሽፈራውና አቶ ብሩክ ከበደ ለነበሩበት ለዚያ ልዑካን በተዘጋጀ አንድ ይፋዊ ያልሆነን የሰሜን አሜሪካ አስተባባሪ ኮሚቴን በሊቀመንበርነት የመምራት እድል አግኝቼ ነበር:: የተደረገላቸው አቀባበል ታሪካዊ ነበር:: በሺህዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በመገኘት ያን የተንጣለለ አየር ማረፊያ ሞሉት:: ሕዝቡንም ለመቆጣጠር ልዩ ቡድን ኃላፊነት ተሰጠው:: እስከ ማረፊያ ሆቴላቸው ድረስ የተከተላቸው ሞተረኛ በጣም ረዥም ርቀት የተለጠጠ ነበር:: በአየር ማረፊያው ግማሽ ክ/ዘመን የሚጠጋ የቆይታ ዘመን ታሪኩ፣ አንዴም እንደዛ ያለ አስደማሚና ታላቅ የአቀባበል ሥነ-ሥርዓት በጭራህ አይቶ አያውቅም:: ፈረንጆቹ፣ « A September to Remember » እንደሚሉት አይነት ነበር::

ብርቱካንንና ልዑካኑን ካገኘሁበት የመጀመሪያዋ ሰዓት አንስቶ በትሁትነታቸው፣ ለመንፈስ ቀለል ያሉ በመሆናቸው፣ በስብዕናቸው፣ ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ ያላቸው ተስፈኝነትና ጭብጦችን ቁልጭ አድርጎ በማስቀመጥ ብቃታቸው በእጅጉ ተነጥቄ ነበር:: እንደዚያ ያለውን ወሳኝ የልዑካን ቡድንን አንዲት ሴት በመምራቷ በርካታ ኢትዮጵያውያን በሀሴታዊ የመደመም መንፈስ ተሞልተው ነበር:: በተከታዮቹ ቀናት ከብርቱካን ጋር የተገናኙ ብዙዎች፣ ማንዴላ አንዴ እንዳሉት ብርቱካን «ሁሌም አስፈሪ ጥምረት የሆኑትን አሪፍ ጭንቅላትና መልካም ልብ» እንዳሏት በመመልከታቸው፣ ለእርሷ የነበራቸው አክብሮትና አድናቆት እጅግ በጣም ልቆባቸው ነበር:: በተናጠልና በጋራ በምትጽፋቸውና በምታደርጋቸው ንግግሮቿ ስለድሮ በጭራሽ አታወሳም፤ ሆኖም ስለመጪዋ ኢትዮጵያ ያላትን ጥልቅ ስጋቶችና ተስፋዎች ታጎላቸው ነበር:: በሚያስደምም መልኩ፣ ለሁለት ዓመታት ያህል በኢ-ፍትሃዊ አካሄድ ስላሰሯትና ስላሰቃዩዋት ሰዎች በጭራሽ አንዳች ጠላትነትና ምሬት አላሳየችም::

## ማነው ብርቱካን ሚዴቅሳን የሚፈራው?

«የተስፋዋ ምድር - ኢትዮጵያ» የሚለው የብርቱካን መርህ ነው:: አምባገነኖቹ ብርቱካንን አይፈሩም፤ ነገር ግን እርሷ በምትወክላቸው - በኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋዎች - ተደነባብረዋል:: ብርቱካን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን አንድነት የምትቆም ነች፤ ብርቱካን የብሔር ቁርሾን፣ መከፋፈልንና ሽኩቻን ለመፋለም የቆመች ነች:: ያ አሳሪዎቿን በድንጋጤ ሽባ የሚያደርጋቸው ነው:: ማንዴላ «ከራሷ ጋር ሰላም ያወረደች አፍሪካ» እንዳለሙት ሁሉ ብርቱካንም ከራሷ ጋር ሰላም ያወረደችና የተስማማች ኢትዮጵያ ሕልሟ ነች:: ያ የአሰቃዮቿን አጥንት ሰርስሮ መቅኔአቸው ድረስ በሚዘልቅ ብርድ እንደጠፈሩ ያደርጋቸዋል:: ብርቱካን፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 70 በመቶ ያህሉን በሚሸፍነው

ወጣት ተቀባይነት አላት:: በጠቅላላው ወጣት የመደመጧ እውነት አምባገነኑን በቆመበት ያደርቀዋል:: የሕግ የበላይነት፣ «የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት»፣ ነፃነት፣ የዴሞክራሲ፣ የእኩልነትና የሰብዓዊ መብቶች መከበርና የተጠያቂነት መኖር ሁሌም ልትከላከላቸው የምትቆምላቸው ናቸው:: ያ አሰቃዬቿ ድንገት ጭንቀት እንዲወራቸው የሚያደርጋቸው ነው::

ብርቱካን እስር ቤት ውስጥ ነች፤ ሆኖም በመላ ኢትዮጵያ ካሉ ሰዎች የላቀ ነፃነት ያላት እሷ ነች:: አምባገነንነትን ተጋፍጣለች፤ አላፈገፈገችም: ሁሉንም ነገር ወርውረውባታል:: በብቸኝነት ታብዳለች ብለው ለብቻዋ አስረዋታል:: መሰረታዊ የሰብዓዊና የሕገ መንግስታዊ መብቶቿን ትዘነጋቸዋለች በሚል ከጠበቆቿ ጋር እንዳትገናኝ ከልክለዋታል:: የድንቁርና ጨለማ ይነግስባታል ብለው መጽሐፍት፣ ሬዲዮና ጋዜጦችን ከልክለዋልታል:: ስሜቷን ለማላሸቅ ባላቸው ተስፋ፣ ከእናቷና ከሴት ልጇ ጋር ሰላምታ መለዋወጧን ከመጨረሷ በፊት የቤተሰቦቿን ጉብኝነት አቋርጠዋል:: ተረስቻለሁ፣ ትተውኛል የሚል ስሜት ያድርባታል በሚል ተስፋ፣ ጓደኞቿና የስራ አጋሮቿ እንዳይጐበኙዋት ከልክለዋታል::

እርሷን ለማዋረድ፣ ለማንኳቀልና ለመተንኮስ ሁሉንም ቆሻሻ የሥነ-ልቦና ጨዋታ ተጫውተዋል፤ ያም መንፈሷን ሰብሮ፣ ጽናቷን አዳክሞ ተስፋ ያስቆርጣትና በሀዘን ይሸብባታል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር:: እስር ቤት ተሰቃይታ ብቻዋን እንደምትሞት ሊያሳምኗት ያላደረጉት ምንም ነገር የለም:: ግና ብርቱካን ተቋቁማዋለች:: ተቋቁማውም ትቀጥላለች፤ ባለድልም ትሆናለች::

ብረት በእሳት እንደሚፈተነው፣ እውነተኛ ፖለቲከኛም በእስር ቤት ይፈተናል:: እስር ቤት የፖለቲካ እስረኛውን የበለጠ ፈርጣማና ጽኑ የሚያደርግ ነው:: ማንዴላ፣ «በእኔ አገር መጀመሪያ እስር ቤት እንኄዳለን ከዘያም ፕሬዝዳንት እንሆናለን» ብለው ነበር:: ብርቱካን ታላላቅ መሪዎች አገራቸውን የማገልገል ግዴታዎችን እንዲወጡ ጥሪ ከመደረጉ በፊት ማድረግ የሚጠበቅባትን እያደረገች ነው የሚል መራከሪያ አለኝ:: ማንዴላ የእድሜ ልክ እስራት በተፈረደባቸው ወቅት፣ በእጣቸው በመማረር የእስር ጊዜያቸውን አላባከኑም:: ከዚያ ይልቅ፣ ሁሉንም ደቡብ አፍሪካውያን ወደአንድነት ለማምጣት በሚጠብቃቸው የአመራርነት ግዴታ ላይ ዝግጅት ለማድረጊያነት ተጠቅመውበታል:: የእስር ጊዜን ለሚጠብቋቸው ከባድ ግዴታዎች መዘጋጃነት መጠቀም የሁሉም የታላላቅ እስረኛ የፖለቲካ መሪዎች የተለመደ ተግባር ነው:: በአሁኑ ሰዓት ብርቱካን ያን እያደረገች ስለመሆኑ አልጠራጠርም:: ሆነም ቀረ፣ የፖለቲካ እስረኞች በመጨረሻ ድል የእነርሱ ነች:: ማንዴላ እንዳሉት፣ እውነት ሀሰትን በመጨረሻ ድል እንደሚነሳ ማመን ለፖለቲካ እስረኞች በድል ከእስር ለመውጣት መሰረታዊው ቅድመ ሁኔታ ነው::

ማንዴላ በአሳሪዎቻቸው ለዓመታት ዝቅ ዝቅ ተደርገው ተንቀዋል፤ ሆኖም ስማቸው በሁሉም ነፃነት በጠማው ደቡብ አፍሪካዊ አፍ ቀድሞ የሚጠራ ነበር:: ማንዴላ እስር ቤት ሳሉ ነበር የሚጠሏቸውን ለመረዳት የተቻላቸውና ከዚህም በላይ ደግሞ ያዘኑላቸው:: የድርድር ጥበባቸውን የበለጠ የሞረዱት:: በደቡብ አፍሪካ ላሉ በጠቅላላ ብለው ለተከተሉት የእኩልነትና የፍትህ ትግል ተጋድሎ ማብቂያ የለሽ ትዕግስት ያደበሩትም በእርስ ቤት ነበር:: የመንግስት ከባባድ ግዴታዎችን እንድትወጣ ለብርቱካን ጥሪ ከመደረጉ አስቀድሞ ልክ እንደማንዴላ አስፈላጊ ሥልጠናን በእስር ቤት እየወሰደች ነው::

ለዴሞክራሲ፣ ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብቶች የሚደረገው ትግል የአጭር ጊዜ ጥረት ነው ብላ ብርቱካን አታምንም:: የብሔር ፖለቲካን ከኢትዮጵያ ለማስወገድ ጊዜና ከፍተኛ ጥረት እንደሚጠይቅ የምታውቀው ነው:: ለዘመናት ጉልበተኛ የበላይ ሆኖ በቆየባት ምድር፣ የሕግ የበላይነትን መርሆችን ለመመስረትና ለመተግበር ቀላል እንደማይሆን ታውቃለች:: ጠንካራ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለመቅረጽ፣ ሊሰራ የሚችል ቅንጅት፣ ሽርክናና ጥምረት መገንባት እጅግ ከባድ ጥረት እንደሚጠይቅ ይገባታል:: ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ድልድይ ለመገንባት የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ወጣት ተሳትፎ እንደሚሻ ትረዳለች::

በቅርብ አቶ መለስ ዜናዊ ብርቱካንን በዘለፉበት ንግግራቸው፣ በምዕራብ ዓለም ያለ ጉልበተኞች ወዲያው ከእስር ያስወጡኛል በሚል እምነት ራሷን እንደሰቀለችው ዶሮ ሆናለች ብለዋል:: አምባገነኑ ብርቱካን በምዕራባውያኑ «እጅግ በጣም ተወዳጅ» እንደሆነችና ትኩረትን ከእርሱ ወስዳለች ብሎ እንደሚያምን አያጠራጥርም:: እንቅጩ፣ ብርቱካን በግለሰብ ደረጃ እንዲደግፏት ወይም መሰረታዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ለማምጣት በዲፕሎማቶች ወይም በምዕራባውያን ግፊት በጭራሽ እምብዛም ተማምና የምታውቅ አለመሆኗ ነው:: ከዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ድጋፍ የመገንባት አስፈላኒቱ ቢገባትም፣ ሁሉም ከባባድ ስራዎች መሰራት ያለባቸው በኢትዮጵያውያን መሆኑን አሳምራ ታውቃለች:-

*«ዲፕሎማሲያዊ ፍልሚያ፣ የአምቢተኝነት ትግል አንድ ዋና አካል ነው ብዬ አስብ ነበር:: እንደሚሉት፣ በፖለቲካ አንድ ሳምንት በጣም ረዥም ነው:: ትምህርቴን ቀስሚያለሁ:: ይህ የእኛ ፍልሚያ ነው:: ስነፃነትና ለፍትህ ፍልሚያውን እንዲቀሳቀሱ እንጠይቃቸዋለን:: ነገር ግን አንለምናቸውም:: ይህ የእኛ ፍልሚያ ነው፤ የእነርሱ አይደለም:: አሸንፈዋል ብለው ሲያስቡ እየሮጡ ይመጣሉ:: . . . አስተዋጽኦአቸውን ማግዘፋችንን ማቆም አለብን:: አሸናፊዎችን ይወዳሉ:: ስትራቴጂካዊ ግቦች አሏቸው፤ እነዚህንም እንዲያሳኩ አሸናፊዎች ብቻ ናቸው ሲረዷቸው የሚታሳቸው:: ለማኞች ሳንሆን አሸናፊዎች መሆናችንን ልናሳያቸው ይገባል::»*

የብርቱካን ስም ሲጠቀስ መለስ በንዴት እንደበቱ ይተሳሰራል:: ፀጉሩ ይቆማል:: በእርሷ ላይ ያለውን ጥልቅ ጥላቻ መቆጣጠር ያቅተዋል:: ከበርማው አምባገነን ጄኔራል ታን ሺው መጽሀፍ አንድ ምዕራብ ያለን ጽሁፍ በመውሰድ በቅርብ በአንድ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፣ «ብርቱካንን ለመልቀቅ ከማንም ጋር በጭራሽ ስምምነት አይኖርም:: በጭራሽ:: አራት ነጥብ:: የሞተ ጉዳይ ነው» ብሎ ነበር:: እዚህ ነጥብ ላይ አቶ መለስ ትክክል ነው:: ማንዴላ እንዳሉት፣ «ነፃ ወንዶች (እና ነፃ ሴቶች) ብቻ ናቸው መደራደር የሚችሉት፤ እስረኞች ውል መግባት አይቻላቸውም:: ብርቱካን የፖለቲካ እስረኛ በመሆኗ ለነፃነቷ «ለመዋዋል» ድርድር ማድረግ አይቻላትም፤ ለነፃነቷም በጭራሽ አትለማመጥም:: «በጭራሽ:: አራት ነጥብ::» አራት ነጥብ!

ኢትዮጵያ፣ ለብርቱካን አታልቅሺ! «እውነቱ በጭራሽ አልተወችሽም:: ቃሏን ጠብቃለች:: አትራቂያት:: አምባገነኖች መንፈሷን ለመስበር፣ አካሏን ለማጉሳቆልና እስር ቤትን ሲኦል ሊያደርጉባት ሁሉንም ነገር ያደርጋሉ:: ማንዴላ የአፓርታይድ አሰቃዬቻቸውን፣ «የደቡብ አፍሪካን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ለማዘግየት ይቻላችሁ ይሆናል፤ ነገር ግን በጭራሽ ማገድ አይቻላችሁም» በማለት ተናግረዋቸው ነበር:: አምባገነኖቹ ብርቱካንንና ሌሎች ሺህዎችን ለፈለጉት ጊዜ ያህል በእስር ለማቆየት፣ ጥቃት ሊያደርሱባቸውና ሰብዓዊነታቸውን ሊያሳጧቸው ይችሉ ይሆናል፤ ሆኖም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ኢትዮጵያን በብር ለመሰነጣጠቅና ሕዝቧን እርስ በእርሱ እንዲዋጋ ማድረግ በጭራሽ አይቻላቸውም:: ከዚያች ጥንታዊት ምድር የዴሞክራሲን፣ የሰብዓዊ መብቶችንና የነፃነትን ድል ለዘላለሙ መቀልበስ አይቻላቸውም::

እትብታችን በተቀበረባት አገራችን ለሰብአዊ መብቶችና ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል እኔና የእኔ መሰሎች ተሳትፎ እንድናደርግ ብርቱካን ስላነቃቃችን በግል አመሰግናታለሁ:: የፈለገ ቢደርስባት እምነቷን ማራመዷ፣ ከተራራ እንደሚፈልቅ ምንጭ በየእለቱ ያድሰናል:: ብርቱካን ላደረገቻቸውና ለሞከረቻቸው በጠቅላላ፣ በዘላለማዊ የምስጋና መንፈስ፣ **"Invictus" (Unconquered)** የሚለውን የዊሊያም ኤርነስት ሄንሌይ ግጥም ግጥም ለእርሷ አውላለሁ:: ማንዴላ በረዥሙ የእስር ጊዜያቸው ይህን ግጥም በብጣሽ ወረቀት ላይ ጽፈው ይዘው መንፈሳቸውን ለማነቃቃት ተጠቅመውበት ነበር:: የማንዴላን መንፈስ እንዳነቃቃው የብርቱካንንም መንፈስ እንደሚያነቃቃ እምነቴ ነው::

## *Invictus*

***Out of the night that covers me,***
***Black as the Pit from pole to pole,***
***I thank whatever gods may be***

*For my unconquerable soul.*

*In the fell clutch of circumstance*
*I have not winced nor cried aloud.*
*Under the bludgeonings of chance*
*My head is bloody, but unbowed.*

*Beyond this place of wrath and tears*
*Looms but the Horror of the shade,*
*And yet the menace of the years*
*Finds, and shall find, me unafraid.*

*It matters not how strait the gate,*
*How charged with punishments the scroll.*
*I am the master of my fate:*
*I am the captain of my soul.*

ብርቱካን በርቺ! አንቺን «የሸፈነው ጨለማ» ለዘላለሙ የሚቆይ አይደለም፡፡ ሁሌም ቢሆን ጨለማ ወደ ብርሃን ይለወጣል፡፡

/አለማየሁ ገብረማሪያም፣በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ፣ ሰንበርናንዲኖ የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰርና የህግ ባለሙያ ሲሆኑ የአለማችን ታዋቂ ሰዎችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ሀሳባቸውን የሚያንሸራሽሩበት «ሃፊንግተን ፖስት» ቋሚ ጸሐፊ ናቸው/